የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

ከውል ውጪ ኃላፊነት በኢትዮጵያ ሕግ የንቃተ-ህግ የስልጠና ሰነድ

በንቃተ ህግ፣ ትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

ታህሳስ 2015 ዓ.ም

ማውጫ

መግቢያ 1

1. የከውል ውጪ ኃላፊነት ምንነት 2

2. በጥፋት ላይ የተመሰረተ ኃላፊነት (Liability for Fault) 4

2.1 በሞያ ሥራ ላይ የሚደረግ ጥፋት 6

2.2 በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም 6

2.3 ስለ መብቶች ግብ 7

2.4 ሕግን ስለመጣስ 7

2.5 የበላይ ትዕዛዝ 8

2.6 የውል አለመፈፀም 9

2.7 ሰውነትን ስለመጉዳት 10

2.8 ነፃነትን ስለመንካት 10

2.9 ስምን ስለማጥፋት 11

3. ጥፋት ሳይኖር ኃላፊነት (Strict Liability) 13

3.1 በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የሚመጣ ኃላፊነት 13

3.1.1 አስፈላጊ ሁኔታ /Necessity/ 13

3.1.2 በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ 14

3.1.3 የስፖርት ስራ 15

3.1.4 አደገኛ ስራ 15

3.2 በንብረት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት 17

3.2.1 እንስሳት ለሚያደርሱት ጉዳት ኃላፊነት 18

3.2.2 በህንፃ ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት 19

3.2.3 በመኪናና ሞተር ተሽከርካሪዎች ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት 21

3.2.4 በተሰሩ እቃዎች ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት 22

3.3 ጥፋት ሳይኖር ለሚኖር ኃላፊነት የሚቀርቡ መከላከያዎች 23

ሀ) የተጎጂው ጥፋት 23

ለ) የውል ግንኙነቶች 24

ሐ) ጥቅም የሌለው ግንኙነት 24

4. ለሌሎች ኃላፊ ስለመሆን (Vicarious Liability) 25

4.1 የወላጆች ኃላፊነት 26

4.2 የመንግስት ኃላፊነት 27

4.3 የአሰሪዎች ኃላፊነት 27
ማጠቃለያ 28
ዋቢ 30

መግቢያ

ኃላፊነት ከውል፣ ከሕግ ወይም ከሞራል ሊመነጭ ይችላል። ከውል የሚመነጭ ኃላፊነት ተዋዋይ ወገኖች በውላቸው መሰረት መፈፀም ሳይችሉ ሲቀሩ ውሉን ያልፈፀመው አካል ለተጎዳው ሊከፍለው የሚገባው ካሳ ወይም ወደነበረበት እንዲመለስ ለማድረግ የሚኖርበት ኃላፊነት ነው። ከሞራል የሚመነጨው ኃላፊነት ደግሞ የሰው ልጆች በራሳቸው ፈቃድ በሕሊናቸው ፈቃድ ሊከውኑት የሚችሉትና አስገዳጅነትም የሌለው የኃላፊነት ዓይነት ነው። ከሕግ የሚመነጭ ኃላፊነት ደግሞ የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት እነዛ ሁኔታዎች በሚሟሉበት ጊዜ ሕጉ በተለያዩ አካላት ላይ የሚጥለው ኃላፊነት ነው። ከሞራል ኃላፊነት በተቃራኒ ከውልና ከሕግ የሚመነጩ ኃላፊነቶች የአስገዳጅነት ባሕሪ ያላቸው ኃላፊነቶች ናቸው።

ከሕግ የሚመነጩ ኃላፊነቶችን የወንጀል ኃላፊነት (ተጠያቂነት) እና የፍትሐብሔር ኃላፊነት ብለን በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን። የወንጀል ኃላፊነት የሚኖረው ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገውን ድርጊት በመፈፀም ሲሆን የፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚፈጠረው ደግሞ በተለያየ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት (ኪሳራ) የደረሰ እንደሆነ ነው። ፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት ውልን መሰረት አድርጎ የሚኖር ኃላፊነት ወይም ከውል ውጪ በሚኖር ግንኙነት የሚፈጠር ኃላፊነት ተብሎ በሁለት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል።

ከውል ውጪ ኃላፊነት እንደአጠቃላይ ከሕግ የሚመነጭ ኃላፊነት ሲሆን በውስጡ ሦስት ዓይነት ኃላፊነቶችን አጠቃሎ ይይዛል። እነዚህም ጥፋትን መሰረት ያደኃላፊነት፣ ጥፋት ሳይኖር የሚኖር ኃላፊነትና ሌሎች ላደረሱት ጉዳት ስለነሱ ኃላፊ የሆኑ ሰዎች የሚኖርባቸው ኃላፊነት ናቸው።

ይህ የስልጠና ሰነድ ከውል ውጪ ኃላፊነትን አስመልክቶ የተዘጋጀ ሲሆን የከውል ውጪ ኃላፊነት ምንነት እና ስለ ሦስቱ የከውል ውጪ ኃላፊነት ዓይነቶችን በተመለከተ የፍትሐብሔር ሕጉን መሰረት አድረጎ ለማብራራት ይሞክራል።

1. የከውል ውጪ ኃላፊነት ምንነት

የሰው ልጅ በኢፌድሪ ሕገ-መንግስት የተጎናፀፋቸው በዓለም አቀፍ ስምምነቶችም እውቅና የተሰጣቸው በርካታ መብቶች አሉት። ከነዚህም ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት፣ የነፃነት መብት፣ የክብርና የመልካም ስም መብት፣ የእኩልነት መብት፣ የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት፣ የመስራትና ሀብት ንብረት የማፍራት መብት እና የአካባቢ ደህንነት መብቶች ተጠቃሾች ናቸው።[1] እነዚህ መሰረታዊ መብቶች ተጥሰው በሚገኙበት ጊዜ በተለያዩ ሕጎች የተለያዩ ውጤት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ለምሳሌ ያክል በወንጀል ሕግ መሰረት የሞት፣ የእስራት እና/ወይም የገንዘብ ቅጣትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ሲሆን በከውል ውጪ ኃላፊነት ሕግ ደግሞ ለተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ ማሰጠትን የሚያስከትሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ኃላፊነት አንድ ሰው ለደረሰ ጉዳት ወይም ለተፈፀመ ጥፋት የሚኖርበትን ተጠያቂነት የሚያመለክት ሲሆን በአጠቃላይ በህግ ሁለት አይነት ኃላፊነቶች ይኖራሉ። እነዚህም የፍታብሄር እና የወንጀል ኃላፊነት ናቸው። የወንጀል ኃላፊነት የሚፈጠረው በወንጀል ህግ ወንጀል ናቸው ተብለው የተደነገጉ ድርጊቶችን በመፈፀም ወይም በወንጀል ህግ እንዲደረግ የታዘዘውን ባለማድረግ በሌላ ሰው ወይም በሀገር ላይ ጉዳት በማድረስ ነው። የወንጀል ኃላፊነት ያለበት ሰው በእስር ወይም ነፃነቱን በማጣት እንዲሁም በገንዘብ ሊቀጣ ይችላል።

የፍትሐብሔር ኃላፊነት የሚፈጠረው በተለያየ ምክንያት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት/ኪሳራ/ የደረሰ እንደሆነ ሲሆን እንዲህ አይነት ኃላፊነት ሁለት ምንጮች አሉት። የመጀመሪያው ከውል የሚመነጭ ሲሆን እንዲህ ዓይነት ኃላፊነት ተዋዋይ ወገኖች በነፃ ፍቃዳቸው የገቡትን ግዴታ በሙሉም ሆነ በከፊል ሳይፈፅሙ ሲቀሩ ነው። ሌላኛው ደግሞ ከውል ውጪ ያለ ኃላፊነት ሲሆን ማንኛውም ሰው የውል ግንኙነት ሳይኖር በህግ በተጠበቀ የሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ሲያደርስ ለዚህ ጉዳት ኃላፊነት የሚወስድበት እና ጉዳት ለደረሰበት ሰው ተገቢውን ካሳ እንዲከፍል የሚገደድበት ስርዓት ነው።

በውል ግንኙነት **የመብት ወይም የግዴታ** ምንጭ የተዋወይ ወገኖች **ስምምነት** ሲሆን ከውል ውጭ ለሚደርስ ሃላፊነት ደግሞ **የግዴታው** ምንጭ **ህግ** ነው።[2] ከውል ውጪ የሚደርስ የጉዳት ኃላፊነት ህግ ዋናው አላማ የተጎዳ ሰውን መካስ ነው። በሌላ በኩል የተጎዳ ሰው ከጉዳቱ ጋር

[1] የኢፌድሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 15፣ 16፣ 17፣ 24፣ 25፣ 26፣ 41 እና 44

[2] የፌደራል የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣ ስለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል፣ *የተሻሻለው ከውል ውጭ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት*፣ ገፅ 7.

በሚመዛዘን መልኩ ወይም ልዩ በሆነ ሁኔታ ለምሳሌ በተበዳዩ ጥፋት እና ሌሎች ካሳን በርትዕ የሚያስወስኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ከጉዳቱ በታች የሆነ ካሳን በመክስ ጉዳቱን ማስወገድ ወይም ማስተካከል ነው።[3] ጉዳት ማለት በህግ በተጠበቁ መብቶች ወይም ጥቅሞች ላይ ኪሳራ ወይም ጉድለት መድረስ ማለት ሲሆን ይኸውም አሁን በግልፅ የሚታይ ጉዳት ወይም ወደፊት በእርግጠኝነት የሚደርስ ወይም የማይታይ የህሊና ጉዳት ሊሆን ይችላል።

ከውል ውጭ ኃላፊነት ምንነት በፍትሐብሔር ሕጉ ትርጉም ያልተሰጠው ቢሆንም ከሕጉ ስያሜ በመነሳት ሦስት ነገሮችን አጠቃሎ የያዘ መሆኑን መረዳት እንደሚቻል የፍትሕ አካላት ማሰልጠኛ ሞጁል ይገልፃል።[4]

> *"የመጀመሪያው ሀሳብ ከውል ውጭ ሲሆን ሁለተኛው ጉዳት የሚለው ነው ሦስተኛው ደግሞ ለዚህ ጉዳት ኃላፊነት የሚመለከት ነው። ስለዚህ ከነዚህ ሦስት ሀሳቦች በመነሳት ሕጉ የውል ግንኙነት ሰይኖር ወይም ውል ላይ ባልተመሰረተ ግንኙነት በአንድ በሕግ በተጠበቀ የሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት ሲደርስ ለዚህ ጉዳት ኃላፊነት የሚያርፍበትን አካል የሚለይና ጉዳቱ በካሳ መልክ እንዲስተካከል የሚያደርግ ሕግ መሆኑን መረዳት ይቻላል"*

እውቁ የብካክስ ሎ የሕግ መዝገበ ቃላትም የሚከተለውን ትርጉም ሰጥቶታል፡- "tort is a civil wrong, other than breach of contract, for which a remedy may be obtained, usu. in the form of damages; a breach of a duty that the law imposes on persons who stand in a particular relation to one another." ይሄንን ወደ አማርኛ ስንመልሰው "ውልን መሰረት ያላደረገ ፍትሐብሔራዊ ተጠያቂነት ሲሆን ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ ወይም የጣሱ ሰዎች በካሳ መልክ ሊከፍሉት የሚገባ ግዴታ ነው" እንደማለት ነው።

በከውል ውጭ ኃላፊነት ሕግ መሰረት ሶስት ዓይነት የኃላፊነት ምንጮች አሉ።[5] የመጀመሪያው የኃላፊነት ምንጭ በራስ ጥፋት በሌላ ሰው ላይ ወይም መብት ላይ ጉዳት ማድረስ (Liability for Fault) ነው። ይህ ጥፋት በቸልተኝነት ወይም ታስቦ እንዲሁም አንድ ድርጊትን በመፈፀም ወይም ባለመፈፀም ሊከሰት ይችላል።[6] እነዚህ ኃላፊነትን የሚያስከትሉ ጥፋቶች በፍታብሔር ህጉ በዝርዝር የተቀመጡ ሲሆን ማንም ሰው አስቦ ወይም በቸልተኝነት ድርጊቶችን በመፈፀም

[3] ዚኒ ከማሁ ገፅ 8
[4] ዚኒ ከማሁ ገፅ 6.
[5] የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2027
[6] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2029

ወይም ባለመፈፀም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆን ጉዳት የደረሰበትን ተነጂ የመካስ የህግ ኃላፊነት ይኖርበታል።

ሁለተኛው የኃላፊነት ምንጭ ምንም ጥፋት ሳይኖር ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት በመውሰድ የሚከሰት (Strict Liability) ነው። በዚህ ዓይነት ኃላፊነት ሕጉ አንድ ሰው ምንም ጥፋት ባይኖርበትም እንኳን ለደረሰው ጉዳት ካሳ የሚከፍልበትን ስርዓት ዘርግቷል።

ሦስተኛው የኃላፊነት ምንጭ ሌላ ሰው ለሚያደርሰው ጉዳት ኃላፊነት በመውሰድ የሚከሰት (Vicarious Liability) ነው። የዚህ ኃላፊነት መሰረቱ የጉዳት አድራሹ እና ኃላፊነትን የሚሸከመው ሰው ህጋዊ ግንኙነት ነው። ይህ ግንኙነት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅና በቤተሰቡ ወይም በልጁ ጠባቂ ወይም አሳዳጊ መካከል፣ በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል፣ በደራሲ እና አሳታሚ መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ያካትታል። ስለሆነም በእነዚህ ህጋዊ ግንኙነት ውስጥ አንድ ሰው በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ጉዳት ሲያደርስ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነትን የሚወስደው ጉዳት አድራሹ ሳይሆን ሕጉ ኃላፊ የሚያደርገው ሰው ነው።

አንድን ሰው በከውል ውጭ ኃላፊነት ተጠያቂ ለማድረግ መሟላት ያለባቸው አራት መርሆች አሉ። እነዚህም ድርጊት/ግድፈት፣ ጉዳት፣ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት እና ያጉዳት በሕግ እውቅና የተሰጠው መሆን የሚሉ ናቸው።[7] ድርጊት ወይም ግድፈት ሲባል አንድ አስቦ ወይም በቸልተኝነት ባደረገው ድርጊት ወይም ግድፈት በሌላ ሰው መብት ላይ ጉዳት ማድረስን ይመለከታል። ለከውል ውጪ ኃላፊነት ዓላማ የሀሳብ ክፍል (አስቦ ወይም በቸልተኝነት) መሟላት አስፈላጊ የማይሆንበት ሁኔታም አለ።[8] ጉዳት ደግሞ በዛ ሰውዬ ድርጊት ወይም ግድፈት ምክንያት የሚከሰት ውጤት ሲሆን ይህ ውጤት ደግሞ በሕግ የተጠበቀ መብትን የሚጥስ ሆኖ ሲገኝ አራተኛውንም መመዘኛ ያሟላል ማለት ነው። የምክንያትና የውጤት ግንኙነት መኖር ሲባልም ያ ደረሰ የተባለው ጉዳት በምን/በማን ምክንያት እንደተከሰተ የሚያሳይ ነው።

2. በጥፋት ላይ የተመሰረተ ኃላፊነት (Liability for Fault)

ይህ የኃላፊነት ዓይነት በፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 2028-2065 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች ነው። ጥፋት ላይ የተመሰረተኃ ኃላፊነት ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከቁጥር 2028-2037

[7] Abdulmalik Abubeker & Desta G/Michael, Extra-Contractual Liability Teaching Material, (2009), p. 2.

[8] Law of torts; https://www.nascollege.org/e%20cotent%2010-4-20/dr%20chandan%20uadhyay/Law%20of%20Torts.pdf (Accessed on 07 Dec. 2022)

ድረስ ያሉት ጠቅላላ ደንቦች በሚል ስር የተመደቡ ሲሆን ከ2038-2065 ድረስ ያሉት ደግሞ ልዩ ሆኔታዎች በሚለው ስር ተመድበዋል።

ጥፋትን መሰረት ያደረገ ኃላፊነት የተለመደና የታወቀ የኃላፊነት ዓይነት ነው። ይህም ማለት ማንም ሰው ባጠፋው ጥፋት መሰረት በሌሎች ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ቢያደርስ ያንን ጉዳት የመመለስ ግዴታ ይኖርበታል ማለት ነው።[9] ጥፋት ማለት ህሊናን ወይም መልካም ጠባይን መሰረት በማድረግ የሚገባን ነገር አለመስራት መስራት የማይገባን ነገር ደግሞ መስራት ስለመሆኑ በሕጉ ተገልጿል። ህሊናን ወይም መልካም ጠባይን የምንለካው ደግሞ ትክክለኛ አእምሮ ያለው ሰው መመዘኛን መሰረት በማድረግ። ከሌሎች ሕጎች በተለይም ከወንጀል ሕግ በተለየ ሁኔታ በከውል ውጪ ኃላፊነት ሕግ የአንድን ድርጊት ወይም ግድፈት ጥፋትነት ለማረጋገጥ የአድራጊውን ዕድሜና የአእምሮውን ትክክለኛነት ግምት ውስጥ ባለማስገባት ነው።[10] ይሄን የምናገኘው የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2030 ላይ ሲሆን በአንድ ድንጋጌ ውስጥ ሁለት እርስ በርሳቸው የሚጋጩ ሀሳቦች ያሉ ይመስላል። አንደኛው በዚሁ ቁጥር ንኡስ ቁጥር ሁለት ላይ የአንድን ድርጊት ወይም ግድፈት ጥፋት መሆን ወይም አለመሆን የሚለካው ትክክለኛ አእምሮ ያለው ሰው መመዘኛን መሰረት አድርገን ነው የሚል ድንጋጌ የያዘ ሲሆን በንኡስ ቁጥር ሦስት ላይ ደግሞ የአጥፊው ዕድሜና የአእምሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ አይገቡም ይላል። የአጥፊዎች ዕድሜና የአእምሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሳይገቡ ድርጊታቸው ወይም ግድፈታቸው ግን ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰው ሚዛን ላይ በማስቀመጥ ጥፋተኝነቱ ይለካል ማለት ትንሽ ፍትሀዊነት የሚጎድለው ድንጋጌ ይሆናል። ለምሳሌ የአንድን አምስት ዓመት ያልሞላው ሕፃን ልጅን ድርጊት ከአዋቂና ትክክለኛ አእምሮ ካለው ሰው ጋር እኩል በመመዘን ጥፋት ነው ወይም ጥፋት አይደለም ማለት ሚዛናዊነት የሚጎድለው ብቻም ሳይሆን ተፈጥሯዊም ያልሆነ አስተሳሰብ ነው። ቢሆንም ከሕጉ ልዩ ባሕሪና ዓላማ አንፃር ማለትም የከውል ውጪ ኃላፊነት ዓላማ የተጎዳን ሰው መካስ ስለሆነ ተጎጂዎችን መካስ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሕጉን ከወተደነገገበት ዓላማ አንፃር ማየቱ ተገቢ ይሆናል።

በጥፋት ላይ የተመሠረተ ኃላፊነትን በዋናነት ከሰው ሰውነት ጋር በተያያዙ መብቶች ላይ የተደረገ ጥፋት፣ በንብረትና በኢኮኖሚያዊ መብት ጋር በተያያዘ የተደረገ ጥፋት እና ሌሎች ብለን መመደብ እንችላለን።

[9] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2028
[10] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2030

2.1 በሞያ ሥራ ላይ የሚደረግ ጥፋት

ይህ የጥፋት ዓይነት በሞያተኛ የሚፈፀም የጥፋት ዓይነት ነው። ስለሆነም ሞያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ሙያ የሚለውን ቃል "በአንድ በተወሰነ ስራ ላይ በልምድ ወይም በስልጠና የሚገኝ እውቀት፣ ችሎታ"[11] ሲል ተርጉሞታል። በመሆኑም የተለየ ስልጠና፣ ክህሎት እና እውቀት የሚያስፈልገው ክወና /activity/ እንደ አሽከርካሪነት፣ የሕክምና ሞያ፣ የአውሮፕላን አብራሪነት፣ ፖሊስነትን[12] ጨምሮ ሞያዎች ሲሆኑ ድንጋይ/አፈር በባሬላ ማጓጓዝ ወይም ከመኪና ላይ ዕቃ መጫን ወይም ማራገፍ ሞያ ሊባል አይችልም።

ሞያ የራሱ የሆነ ሕጎች ወይም መመሪያዎች አሉት። አንድን ሞያዊ ስራ ለመከወን የሞያውን ሕጎች /rules/ ማየትና መተግበር ያስፈልጋል። እነዚህ ሕጎች በፅሑፍ የተቀመጡ ወይም ያልተፃፉ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የመኪና መንዳት ሞያ ሕጐች በፅሁፍ ያሉ ናቸው። እነዚህን የተፃፉ ሕጐች እያንዳንዱ አሽከረካሪ አውቋቸው በዛው መሠረት መኪናውን ማሽከርከር ይጠበቅበታል።[13] እንዲሁም በሕግ ላይ በትክክል ተገልጸ የተመለከተውን ልዩ ድንጋጌ ልዩ ደንብና ስርዓት መጣስ በጥፋትነት የሚፈረጅ ስለሆነ ኃላፊነትን የሚያስከትል ሲሆን ሕግን አለማወቅም ከተጠያቂነት የሚያድን አይሆንም።[14]

2.2 በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም

በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም ከሙስና ወንጀሎች[15] ዋነኛ መገለጫዎች አንዱ ከመሆንም ባለፈ በፍትሐብሔር ሕጉ የከውል ውጭ ኃላፊነት ምንጭም ሊሆን ይችላል። በፍትሐብሔር ሕጉ መሰረት ሁለት የስልጣን ዓይነቶችን እናገኛለን።[16] አንደኛው ዓይነት ስልጣን የግለሰብ ጥቅምን ለመጠበቅ /Interest of a given private individual/ የተሰጠ ሥልጣን ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ደግሞ ለጠቅላላው ጥቅም እንዲያገለግል /In the interest of the public/ የተሰጠው ስልጣን ነው። ለመጀመሪያው ዓይነት ስልጣን ምሳሌ የሚሆነን በተለያየ ምክንያት ችሎታ ያጡ ሰዎችን (እንደሕፃናት፣ አረጋውያን ወይም የአእምሮ

---

[11] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ) *አማርኛ መዝገበ ቃላት* (የካቲት 1993) ገፅ 68

[12] የፌደራል ሰበር ሰሚ ውሳኔዎች ቅፅ 23 መዝገብ ቁጥር 142630

[13] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2031(1)

[14] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2035

[15] የሙስና ወንጀሎችን ለመቆጣጠርና ለመከላከል የወጣ አወጅ ቁጥር 881/2007 አንቀፅ 9

[16] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2033

ሕሙማን) ጥቅም ለመጠበቅ ለአሳዳሪውና ለሞግዚት የተሰጠ ስልጣን ሲሆን ለሁለተኛው ደግሞ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ (ዳኛ፣ ዓቃቤ ሕግ፣ ሀኪም ወዘተ) ያላቸው ስልጣን ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

በየትኛውም ዓይነት ስልጣን ቢሆን አንድ ሰው የተሰጠውን ስልጣን ለግል ጥቅሙ የሠራበት እንደሆነ በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም ጥፋት ፈፅሟል ያስብላል። በሁለተኛው የስልጣን ዓይነት የመንግስት ሠራተኛው በሹመት ያገኘውን ስልጣን ያለአግባብ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ካዋለውም በስልጣኑ ያለ አግባብ ተጠቅሟል ይባላል። ሁለቱም ዓይነት በስልጣን ያለ አግባብ መጠቀም ጥፋት ናቸው።

2.3 ስለ መብቶች ግብ

የሰው ልጆች በመብቶቻቸው ሲጠቀሙ ያሉባቸውን ገደቦችም ግምት ማስገባትና መጠበቅ ይኖርባቸዋል። መብቴ ነው ብሎ እንደፈለጉ መሆን ከገደብ ያልፍና ተጠያቂነትም/ኃላፊነትም ሊስከትል ይችላል። በእርግጥ አንድ ሰው ባለው መብት ከኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ፋይዳ ውጭ ተጠቅመህበታል ተብሎ ተጠያቂ ማደረግ አይቻልም።[17] ለምሳሌ አንድ ሰው ያለውን ትርፍ ቤት ለማንም ሳያከራይ ወይም ማንንም በነፃ ሳያኖር ቆልፎ ቢያስቀምጠው ሰውዬው ባለው መብት ተጠቅሞ ቤቱን ከኢኮኖሚያዊ ወይም ማሕበራዊ ፋይዳ ውጭ አድርጎታል። ይህ አድራጎት በመደበኛው የነገሮች አኳኋን (in normal course of things) የሚያስጠይቀው ተግባር አይደለም። ነገር ግን ይህ ሰው ድርጊቱን ያደረገው ሌሎችን በመጉዳት ሀሳብ ከሆነ ድርጊቱ በጥፋትነት ተቆጥሮ ኃላፊነትን ያስከትልበታል።[18] ለምሳሌ አንድ የታክሲ ባለንብረት መኪናው እንዳይጎዳበት እያሳረፈ የመስራት መብት ያለው መሆኑ እሙን ቢሆንም ሆን ብሎ በሰራተኞች መውጪያና መግቢያ ሰዓት እየጠበቀ መኪናውን የሚያቆማት ከሆነ ህዝብን ወይም መንግሰትን ለመጉዳት ያደረገው ድርጊት ስለሆነ ኃላፊነትን የሚያስከትል ጥፋት ይሆናል ማለት ነው።

2.4 ሕግን ስለመጣስ

በሕግ በግልፅ የተፃፈን ነገር መጣስ ኃላፊነትን ሊያስከትል ይችላል። ዋናው መታየት ያለበት ጉዳይ ኃለፊነትን የሚስከትል ድንጋጌ ግልፅ እና አሻሚነት የሌለው መሆን ይገበዋል።[19] ሕግ

---

[17] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2034

[18] ዚኒ ከማሁ (ከዚህ በላይ የተደነገጉት ቁጥሮች ሳይነኩ ... ሲል በመጉዳት ሀሳብ የተደረገ ድርጊት ሁሉ ጥፋት ስለመሆኑና ጥፋትን ያደረገ ደግሞ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ የሚያመለክቱ ናቸው ከዚህ በላይ ያሉት ቁጥሮች)

[19] የግርጌ ማስወገጃ 7 ገፅ 37-38

ስንል ሕግ ለማውጣት ስልጣን በተሰጠው አካል የወጣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ማለታችን ነው። በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2035 ላይ የተጠቀመበት አገላለፅ ልዩ ድንጋጌ፣ ልዩ ደንብና ስርዓት በማለት ሲሆን አዋጅ፣ ደንብ ወይም መመሪያን መጣስ የተመለከተ እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይባል። ከነዚህ የሕግ ማዕቀፎች ውጪ ያለ ማንኛውም ነገር አስገዳጅነት ኖሮት ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስላልሆነ የድንጋጌውን ይዘት ሕግ ለማውጣት ስልጣን ባለው አካል የወጡ ሕጎች በሚል መንፈስ ልንገነዘበው ይገባል።[20]

2.5 የበላይ ትዕዛዝ

የበላይ ትዕዛዝን አስመልክቶ ሶስት የተለያዩ መነሻዎች አሉ። የመጀመሪያው ሁሌም ሕግን ብቻ ታዘዝ (always obeying the law) የሚለው ሲሆን ይህ ማነሻ ሁሌም ሰው ሕግን ያውቃል የሚለውን ግምት መሠረት ያደረገ ነው። ይህ መነሻ ብዙ ጊዜ ለክርክርና ለጭቅጭቅ ይዳርጋል እየተባለ ይተቻል።[21]

ሁለተኛው መነሻ ደግሞ ሕግን እርሳው አለቃህን ብቻ ታዘዝ (obeying the order and forgetting the law) የሚል ነው። ይህ ደግሞ አለቆች ሕግን በደንብ ያውቃሉ የሚል ግምትን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ መነሻ በሠራዊቱ ውስጥ ጥሩ ሊሆን የሚችል ቢሆንም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በሰው እና በንብረት ላይ በደረሰው ስቃይና ውድመት ይህ መነሻ ተተችቷል። ምክንያቱም ወታደሮች በሰው ልጅ ላይ በዛን ጦርነት ጊዜ የደረሰውን እልቂትና ግፍ የፈፀምነው ከላይ ትዕዛዝ ስለተሰጠን ነው በማለታቸው ነበር።[22]

ሶስተኛው መነሻ ሕጉንም አለቃህንም ታዘዝ (obeying both the law and the order) የሚለው ነው። በፍትሐብሔር ሕጋችን ቁጥር 2036 መሰረት ይኼኛውን መነሻ የተከተለ ይመስላል።[23] በዚህ ድንጋጌ መሠረት በመጀመሪያ ትዕዛዙን በሚሰጠውና ትዕዛዙን በሚቀበለው መሀል የአለቃና የምንዝር ግንኙነት ሊኖር ይገባል። የዚህ ድንጋጌ አጠቃላይ ይዘት ሲታይ በመርህ ደረጃ በበላይ ኃላፊ ቀጥተኛ ትእዛዝ ስር ሆኖ የተፈፀመ ጥፋት ከተጠያቂነት የማያድን መሆኑን በተለይም የበላይ ኃላፊው ያንን ትእዛዝ የመስጠት ችሎታ የሌለው ከሆነና ትእዛዙ የአመፅ ጠባይ (ሕገ-ወጥ) ካለው ወይም ተገቢነት የሌለው (አስወቃሽ)

[20] ዚኒ ከማሁ
[21] ዚኒ ከማሁ ገፅ 38-39
[22] ዚኒ ከማሁ
[23] ዚኒ ከማሁ

ከሆነ አድራጊው ጥፋት ጥፋት እንዳደረገ ተወስዶ ለድርጊቱ ኃላፊ ይሆናል።[24] እንዲህ በሚሆን ጊዜ ታዛዡ በወንጀል ሕግም ጭምር ተጠያቂ ከመሆን አያመልጥም።[25]

አጥፊው ከኃላፊነት ሊያመልጥ የሚችለው ትዕዛዝ ፈፃሚው ጥብቅ በሆነ በመንግስታዊ ወይም በወታደራዊ ዲስፕሊን ምክንያት በተሰጠው ትዕዛዝ ለመከራከር ወይም ያንን የታዘዘውን እንጂ ሌላ ነገር ለማድረግ በማይችልበት ሆኔታ ውስጥ ያደረገው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው።[26]

2.6 የውል አለመፈፀም

አንድ ሰው በገባው ውል መሠረት ግዴታውን አለመፈፀሙ ከውል ውጭ አላፊነት ስር ጥፋተኛ አያሰኘውም። ከሣሽ ለክሱ መሠረት ማድረግ ያለበት ስለውል አለመፈፀም የሚደነግጉትን ድንጋጌዎች ነው። አንዳንድ ጊዜ ግን የትኛውን /ከውል ውጭ ወይስ የውል/ ድንግጌ ነው ለክሳችን መነሻ ማድረግ ያለብን የሚለው አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ ያጋጥመናል። ለምሳሌ በቁጥር 2533 መሠረት ሠራተኛው የሥራ ውል ካለቀ በኋላም ቢሆን በሥራው ጊዜ ያወቃቸውን የአሰሪውም ምስጢሮች መጠበቅ እንዳለበት ተደንግጓል። ሠራተኛው ይህን ቁጥር ጥሶ ቢገኝ ተጠያቂ የሚሆነው በየትኛው ሕግ መሠረት ነው? በውሉ መሠረት ነው እንዳንል የስራ ውሉ ተቋርጧል። ቁጥር 2035ን ተጠቀምን በከውል ውጭ ኃላፊነት እንደንጠይቀው ደግሞ በቁጥር 2037 መሰረት ውልን ተከትሎ ለሚደርስ ጉዳት በውሉ ደንብ ካልሆነ በስተቀር በከውል ውጭ ኃላፊነት ሕግ አይስጠይቅቸም ይለናል። ቢሆንም አንዳንድ ሰዎች በሁለቱም የሕግ ማዕቀፎች መከራከር እንደሚቻል ያምናሉ። አንደኛው ውል ቢቋረጥም ሠራተኛው የአሰሪውን ሚሰጢር ከውሉ መቋረጥ በኋላም እንዳያወጣ በሕግ ግዴታ ተጥሎበታል። ስለሆነም ሠራተኛው ሚስጥሩን ቢያወጣ ግልፅ የሆነን ሕግ አንደጣሰ ተቆጥሮ በቁጥር 2035 መሠረት ተጠያቂ ልናደርገው እንችላለን ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ ምንም እንኳን በአጠቃላይ ውሉ ቢቋረጥም ምስጢር ያለማውጣት ግዴታው ግን ይቆያል/Persist/። ስለሆነም ሚስጢር

[24] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2036(1)(2)

[25] የኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 74 *(ትእዛዝ ፈፃሚው ከሕግ ውጭ መሆኑን በተለይም አዛዡ ለማዘዝ ስልጣን የሌለው ወይም ድርጊቱ ወንጀል መሆኑን እያወቀ፣ የፈፀመውም ድርጊት የነፍስ መፈግደል ወይም የቃጠሎ ወይም በሰዎች ላይ ወይም በንብረት ወይም በሕብረተሰብ ዋና ዋና ጥቅሞች ላይ ወይም በዓለም አቀፍ ሕግ ላይ የደረሰ ከባድ አደጋ ሲሆን በጥፋቱ ኃላፊ ሆኖ ይቀጣል።)*

[26] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2036(3)

ሲያወጣ ያለማድረግ ግዴታውን /Obligation not to do/ እንደጣሰ ተቆጥሮ በውል ሕግ ቁጥር መሠረት ተጠያቂ ልናደርግው እንችላለን ይላሉ።[27]

2.7 ሰውነትን ስለመጉዳት

አስበነውም ሆነ በድንገት የሌላ ሰውን ሰውነት መንካት የተለመደና ብዙ ጊዜ የሚያጋጥመን ክስተት ነው። ሆኖም በሕግ ዓይን ሲታይ ይህ ድርጊታችን ኃላፊነትን የሚያስከትል ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። ማንም ሰው አስቦ ያለሰውየው ፈቃድ የሌላ ሰውን አካል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የነካ እንደሆነ በጥፋትነት ተቆጥሮ የፍትሐብሐር ኃላፊነት ይኖርበታል።[28] ቢሆንም በልዩ ሁኔታ መንካት የሚፈቀድባቸውና አድራጊውም ጥፋተኛ ተብሎ ኃላፊነት የማይጣልበት ጊዜ አለ።[29] እነዚህም፡-

- ✓ ተበዳይ የሚቃወም መሆኑን በአእምሮው ግምት ሊያስበው የማይችል ከሆነ (ለምሳሌ ቤተሰብ ከሆኑ)
- ✓ ድርጊቱ የተፈፀመው እራሱን ወይም ሌላ ሰውን ወይም ንብረቱን ለመከላከል ከሆነ
- ✓ ልጁን፣ የአደራ ልጁን፣ ተማሪውን ተገቢ ቅጣት ለመቅጣት ከሆነ፤ በእርግጥ ይህ ድርጊት ከወንጀል ተጠያቂነት አንፃር ሲታይ የሚጋጭ ወይም ግርታን የሚፈጥር ነገር ያለው ሊመስል ይችላል። ሆኖም በወንጀል ሕጉ የተከለከለው ልጅን (ሕፃናትን) መምታት፣ ከአቅም በላይ ማሰራት፣ መበደል ወይም ችላ ማለት እንጂ ለሕፃናት መልካም አስተዳደግ ሲባል ሕግን የማይቃረን የድስፕሊን እርምጃን አያካትትም።[30]
- ✓ ተበዳዩ የአእምሮ መታወክ ሕመም ያለበት ከሆነና ጉዳት እንዳያደርስ በማሰብ የተደረገ ከሆነ እና የመሳሰሉት ምክንያቶች ሲኖሩ

2.8 ነፃነትን ስለመንካት

ከግለሰቡ ፈቃድ ውጭ የሌላውን ሰው ነፃነት የሚጋፋ ተግባር መፈፀም ጥፋት በመሆኑ ኃላፊነትን የሚያስከትል ተግባር ነው።[31] የሌላውን ነፃነት መንካት ሲባል በሰውነቱ ላይ ጉዳት ቢያደርስም ባያደርስም የሰውዬውን ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብቱን ማገድ ወይም አንዳች አደጋ እንደሚደርስበት በመዛት የግዴታ ስራ እንዲሰራ የማስገደድ ተግባርን ያጠቃልላል።

---

[27] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 41-42
[28] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2038
[29] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2039
[30] የግርጌ ማስታወሻ 25 አንቀፅ 576
[31] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2040

የሰውን ነፃነት መንካት በጥፋትነት ተቆጥሮ ኃላፊነት የማያስከትለው በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች የተፈፀመ ከሆነ ብቻ ነው፡-[32]

- ✓ ተከሳሹ ይህን ያደረገው ሕግ በሚፈቅድለት ስልጣኑ ምክንያት ሲሆን
- ✓ ነፃነቱ የተነካበት ሰው ወንጀል ሰርቷል ብሎ ለማሰብ በቂ ምክንያት ሲኖር እና
- ✓ በባለስልጣናት አንድ የተወሰነ ቦታ ብቻ እንዲቀመጥ የታዘዘ ሰው ከዚህ ግዴታው ለማምለጥ መሰናዳቱን የሚያሳይ በቂ ምክንያት ሲኖር የሚሉት ናቸው

2.9 ስምን ስለማጥፋት

የሌላን ሰው ስም ማጥፋት በጥፋትነት የሚቆጠር ተግባር ነው። የህም አንድ ሰው በንግግሮቹ፣ በፅሑፎቹ ወይም በሌላ ዓይነት አድራጎቶቹ በሕይት ያለን ሰው ስም ያጠፋ እንደሆነ በፍትሐብሔር ኃላፊነትን ያስከትልበታል። በዚህም አድራጎቱ ጥፋተኛ ነው ለማለት ስሙ የጠፋበት ሰው በሕይዎት ያለ ሰው ሆኖ፣ እንዲጠላ፣ እንዲዋረድ፣ እንዲሳቅበትና ሰዎች በሱ ላይ ያላቸው እምነት እንዲቀንስ እንዲሁም ዝናውና የወደፊት እድሉ እንዲበላሽ የሚያደርግ ተግባር መሆን አለበት።[33] ከዚህም በተጨማሪ ስም አጥፊ ንግግሩ ወይም ፅሑፉ ስሙ የሚጠፋበትን ሰው ስም በግልፅ መግለፅ ያለበት ሲሆን አድራጊው ድርጊቱን ያደረገው ተበዳዩን ለመጉዳት አስቦ ባይሆንም እንኳን ኃላፊነቱን አያስቀረውም።[34] የሚከተሉት ተግባራት የስም ማጥፋት ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ፡-[35]

- ✓ ባልፈፀመው ተግባር ወንጀል ሰርቷል ብሎ መበደል (ስምን ማጥፋት)
- ✓ በሞያ ስራው ችሎታ የሌለው ወይም እውነተኛነት የሌለው መሆኑን ለማሳመን የተደረገ ስም ማጥፋት
- ✓ ነጋዴው ውጤታማ እያለ እዳውን መክፈል እንደማይችል አድርጎ ስም ማጥፋት
- ✓ ተላላፊ በሽታ አድሮበታል በማለት አስመስሎ ለማሳመን መጣር
- ✓ አስነዋሪ የሆነ ጠባይ አለው በማለት አስመስሎ ለማሳመን መጣር

በስም ማጥፋትና በስድብ መካከል ልዩነት አለ? አለ ካሉ ልዩነታቸውን ይግለፁ።

[32] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2041-2043
[33] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2044
[34] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2045
[35] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2109

ምንም እንኳን በውጤት (የሚያስከትሉት ጉዳት) ደረጃ ያን ያክል ልዩነት አለ ባይባልም በአፈፃፀማው እና በሚገዙበት የሕግ ዓይነት ላይ ልዩነት ይኖራቸዋል። በአፈፃፀም ደረጃ ስናይ ስም ማጥፋት ኃላፊነትን ሊያስከትል የሚችለው ለሦስተኛ ወገን ሲገለፅ[36] ሲሆን ስድብ ግን በቀጥታ[37] ለተበዳዩ የተነገረ መሆን አለበት።

የስም ማጥፋት ተግባር ቢፈፀምም የድራጊው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማስረዳት ከቻለ ከኃላፊነት ነፃ ይሆናል፡-[38]

- ✓ ድርጊቱ የተፈፀመው ለሕዝብ ጥቅም ሲባል እንደሆነ
- ✓ የተገለፀው የስም ማጥፋት ሀሳብ ሀሰትን መሆኑን ሳያውቅ የደረገው ከሆነ (እውነት ነው ብሎ ባመን የጠፈፀመ)
- ✓ ጉዳዩ እውነት መሆኑ ከተረጋገጠና ተበዳዩን ለመጉዳት ያልተደረገ ከሆነ
- ✓ ስም ማጥፋቱ የተደረገው በምክር ቤት (በፓርላማ) ክርክር፣ በፍርድ ቤት ክርክር ጊዜ ሆኖ ተበዳዩን ለመጉዳት ያልተደረገ ከሆነ
- ✓ በጋዜጣ ታትሞ የተወራ የስም ማጥፋት ተግባር ተደርጎ ከሆነ
    - አጥፊው በተለይ ተበዳዩን ለመጉዳት አስቦ ያላደረገው ከሆነ
    - ከፍ ባለ ቸልተኛነት ያልተደረገ ከሆነ
    - በተበዳዩ ጠያቂነት አጥፊው መልሶ ይቅርታ ከጠየቀ

ትዳር ወይም ጋብቻ ማሕበራዊ ተቋም ነው። የጋብቻ መፍረስ የሚያስከትለው ማሕበራዊ ቀውስም ግልፅ ነው። በመሆኑም ጋብቻ በተለያዩ ሕጎች ጥበቃ ተሰጥቶት እናገኛለን። ከነዚህም መካከል የፍትሐብሔር ሕጉ በከውል ውጪ ኃላፊነት የሰጠውን ሽፋን ማየት ይቻላል። በዚህም መሰረት አንዲት ባለትዳር የሆችን ሴት ባሏን ጥላ እንድትሄድ ቁርጥ ውሳኔ ላይ እንድትደርስ ያደረገ ሰው ወይም አንድን ባለትዳር ወንድ ሚስቱን ጥሎ እንዲሄድ ያደረገ እንደሆነ ጥፋት አለበት ይላል ሕጉ[39]። ሕጉ ከዚህም አልፎ የሰው ሚስት የሆነችን ሴት ያለባሏ ፈቃድ እቤቱ ተቀብሎ ማስቀመጥ ወይም ማስተነገድም በጥፋትነት እንደሚቆጠር ይደነግጋል።[40] ይህ ድንጋጌ በሁለት ምክንያቶች የተሳሳተ(ተገቢነት የሌለው) የመስላል። አንደኛው አንድን ሰው ወንድም ሆነ ሴት በቅን ልቦና ተቀብሎ ማስተናገድና መርዳት የሰብአዊነት ዋነኛ መገለጫ

[36] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 55
[37] የግርጌ ማስታወሻ 25 አንቀፅ 615
[38] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2046-
[39] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2050
[40] ዚኒ ከማሁ

ሆኖ የሚወሰድ እንጂ አስወቃሽ ሊሆን አይገባም። ሁለተኛው ደግሞ በሕጉ ሴት ተቀብሎ ማስቀመጥ ወይም ማስተናድ ክልክል መሆኑ ሲታይ ለምን ሴትን ብቻ? የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ የእኩልነት መርህን የጣሰ ድንጋጌ ነው ማለት ይቻላል።

ሆኖም አንዲትን ሴት ለመርዳት በርህራሄ የተደረገ እርዳታን ሕጉ ሙሉ ለሙሉ ዝግ አላደረገውም። ይህም ባልና ሚስቱ ተለያይተው ለመኖር ከወሰኑ ወይም ባልየው ሚስቱን እያሰቃያት ወይም ግፍ እየፈፀመባት በመሆኑ በሰብአዊነት ተነሳስቶ የሚደረግ እርዳታ የተከለከለ አይደለም።[41]

3. ጥፋት ሳይኖር ኃላፊነት (Strict Liability)

የፍትሐብሔር ህግ በቁጥር 2027/2/ አንድ ሰው ጥፋት ባልሆነ ስራ በህጉ እንደተመለከተው በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስራ ከሰራ ወይም በእጁ ያየዘው ነገር በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ኃላፊ እንደሚሆን ይደነግጋል። ስለሆነም አንድ ሰው ምንም የፈፀመው ጥፋት ሳይኖር ሕጉ በዘረዘራቸው አድራጎቶች ኃላፊነት ሊወስድ ይችላል። ጥፋት ሳይኖር ኃላፊነት በፍትሐብሔር ህጉ ከቁጥር 2066-2089 ስር በዝርዝር የተቀመጡ ሲሆን እነዚህንም በአጠቃላይ አንድ ሰው በሚፈፅመው ድርጊት ምክንያት የሚመጣ ኃላፊነት እና በንብረት ባለቤትነት ወይም ባለይዞታነት ምክንያት ንብረቱ ጉዳት ሲያደርስ የሚመጣ ኃላፊነት በማለት ልንከፍላቸው እንችላለን።

3.1 በተፈፀመ ድርጊት ምክንያት የሚመጣ ኃላፊነት

3.1.1 አስፈላጊ ሁኔታ /Necessity/

አስፈላጊ ሁኔታ የሚባለው የራስን ወይም ሊከላከሉለት የሚገባን የሌላውን ሰው ህጋዊ መብት ሊደርስ ከሚችል ከፍተኛ አደጋ ለማዳን በሌላ ሰው ህጋዊ መብት ላይ ሆነ ብሎ ጉዳት ማድረስ ነው። በአስፈላጊ ሁኔታ ስር ሆኖ ጉዳት ማድረስ ምንም እንኳን ጉዳት የደረሰው ሆነ ተብሎ በተፈፀመ ድርጊት ቢሆንም አደጋውን ለማስቀረት የተፈፀመ በመሆኑ እንደ ጥፋት ስለማይቆጠር የወንጀል ተጠያቂነትን አያስከትልም።[42] በኢፌዲሪ የወንጀል ሕግ በአንቀፅ 75 ስር የመጀመሪያው ንባብ *"የራስን ወይም የሌላ ሰውን መብት በቅርብ ከሚደርስ ከባድ ከሆነ አደጋ ለማዳን የተፈፀመ ድርጊት፣ አደጋውን በሌላ መንገድ ማስወገድ የማይቻል ከሆነና*

[41] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2051
[42] የግርጌ ማስታወሻ 25 አንቀፅ 75

አድራጊው ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ ዘዴዎችን የተጠቀመ ከሆነ አያስቀጣም" በማለት ደንግጓል። ነገር ግን ምንም እንኳን ድርጊቱ ጥፋት ባይሆንም በድርጊቱ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስለሚኖሩ ይህ ድርጊት የፍታብሔር ተጠያቂነትን ማስከተሉ አይቀርም።

የፍትሐብሔር ህጉም በቁጥር 2066/1/ ስር ማንም ሰው ራሱን ወይም ሌላውን ሰው በአካልም ሆነ በንብረት ላይ በእርግጥ ከሚደርስ አደጋ ለመከላከል ብሎ በሌላ ሰው ላይ ሆነ ብሎ ጉዳት ያደረሰ እንደሆን ኃፊነትን እንደሚወስድ እና ለተጎጂውም ካሳ የመክል ግዴታ እንደሚኖርበት ያቀምጣል። ሆኖም ይህ ድርጊት ጥፋት አይደለም ተብሎ በአስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ሊካተት የሚችለው ከአደጋ የሚተርፈውና ጉዳት የሚደርስበት መብት ሲነፃፀሩ የሚተርፈው መብት ሚበልጥ ከሆነ ነው።[43] ይህ ካልሆነ ድርጊቱ ጥፋት ስለሚሆን በዚህ ርእስ ስር የሚካተት አይሆንም ማለት ነው።

3.1.2በሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ

የፍትሐብሔር ህጉ በቁጥር 2067(1) ስር እንደሚያስቀምጠው ማንም ሰው በሰራው ስራ ወይም በድርጊቱ በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ካደረሰ ድርጊቱ ጥፋት ባይንም እንኳን ላደረሰው ጉዳት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ይኖርበታል። ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰው በሚከተሉት ሁኔታዎች ከሆነ ጉዳት አድራሹ ተጠያቂ አይሆንም።[44] እነሱም፡-

- ✓ ጉዳት ያደረሰው ስራ በህግ የተፈቀደ ወይም የታዘዘ እንደሆነ፤ ለምሳሌ በፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ የወጣበት ሰው በፖሊስ ለመያዝ ፈቃደኛ ባይሆንና ቢያስችግር ፖሊሱ ተመጣጣኝ ሀይል እንዲጠቀም ህግ ይፈቅድለታል። በዚህ ወቅት ተጠርጣሪው የአካል ጉደት ቢደርስበት ፖሊሱ ኃላፊነት አይኖርበትም።
- ✓ ጉዳቱ የደረሰው ራስን ለመከላከል በተፈፀመ ድርጊት ከሆነ፤ ለምሳሌ አንድ ሰው ጉዳት ሊያደርስበት የመጣን ሰው ቀድሞ በመከላከል ሰውየው ላይ ጉዳት ካደረሰ ለጉዳቱ ተጠያቂ አይሆንም።
- ✓ ጉዳቱ የደረሰው በተጎጂው ጥፋት ከሆነ ይህም ማለት የጉዳቱ ምክንያት ተጎጂው ብቻ ከሆነ እና የጉዳት አድራሹ አስተዋፅኦ ከሌለ ጉዳት አድራሹ ምንም አይነት ተጠያቂነት አይኖርበትም። ለምሳሌ ሌባን ለመያዝ በተደረገ ግብግብ (ፍትጊያ) ሌባው የአካል ጉዳት ቢደርስበት የንብረቱ ጠባቂ ኃላፊነት አይኖርበትም።

[43] የግርጌ ማስወሻ 7 ገፅ 86
[44] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2067(2)

3.1.3የስፖርት ስራ

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2068 ላይ አንድ ሰው የስፖርት ስራ (ጨዋታ) በመስራት ላይ ሳለ ሌላውን ተጫዋች ወይም ተመልካች ቢጎዳው በስፖርት ስነ-ስርዓት የተመለከተውን ደምብ በግልፅ ካልጣሰ ወይም የተንኮል ስራ ካልፈፀመ በቀር ኃላፊነት የለበትም በማለት የደነግጋል። የዚህን ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ ወይም ትርጉም ብንመለከት ጉዳት አድራሹ የስፖርቱን ደምብ ከጣሰ ወይም ጉቱን ያስከተለው በተንኮል ከሆነ ተጎጂውን የመካስ ፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን እንረዳለን። ለምሳሌ አንድ የእግር ኳስ ተጫዋች በሜዳ ውስጥ በመጫወት ላይ ሳለ ኳሱን ሆን ብሎ ወደ ተመልካች በመምታት በአንድ ተመልካች ላይ የሆነ ጉዳት ቢያደርስ ኃላፊነት ይኖርበታል። ነገር ግን ኳሱን ለጓደኛው ለማቀበል፣ ጎል እንዳይቆጠርበት ለመከላከል ወይም ለማስቆጠር በማሰብ በመምታቱ መክንያት በተጫዋችም ሆነ በተመልካች ላይ ጉዳት ቢያደርስ ሊጠየቅ አይችልም።

የጨዋታውን ሕግ አክብሮ እስከተጫወተ ድረስ ጉዳት ቢያደርስም እንኳ ተጠያቂነት የለበትም፤ ነገር ግን ጉዳት ያደረሰው ግልፅ ደንብን በመጣስ ወይም በተንኮል ከሆነ ኃላፊነት አለበት የሚለው አገላለፅ በእርግጥ ጥፋት ሳይኖር ኃላፊነት ነውን?

3.1.4አደገኛ ስራ

ጥፋት ባይሆኑም በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ቢያደርሱ ኃላፊነትን የሚያስከትሉ ናቸው ተብለው በአደገኛነት የተፈረጁ አራት የስራ ዘርፎች አሉ።[45] እነዚህም፡-

- ✓ የሚፈነዱ ወይም መርዝ የሚሆኑ ቅመማትን በስራ ላይ ማዋል
- ✓ ከፍተኛ ጉልበት ያው የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት
- ✓ የመሬትን የተፈጥሮ መልክ መለወጥ
- ✓ አደገኛ የሆነ የኢንዱስትሪ ስራ ማካሄድ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩ አደገኛ ስራዎችን መስራት ጥፋት አይደለም። ይልቁንም ስራዎቹ ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ግንባታ የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ በመሆኑ አደገኛ በመሆናቸው ብቻ ሊከለከሉ አይችሉም። ነገር ግን ከስራዎቹ ባህሪ አንፃር ለሕብረተሰቡ ክፍተኛ የሆነ የአደጋ ስጋት በመሆናቸው ሕጉ እነዚህ ስራዎች ከሚያደርሱት ኪሳራ ለመጠበቅ ከለላ ይሰጣል። ስለሆነም በእነዚህ ስራዎች ምክንያት በሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ከደረሰ የሠራው

[45] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2069

ባለቤት ጥፋት ባይኖርበትም ለተጎጂው የመካስ ኃላፊነት ይኖርበታል። ሕጉ ይህን አማራጭ የወሰደበት ምክንያት እነዚህ ስራዎች በተፈጥሮአቸው ግዙፍ በመሆናቸው እና የባለቤቶቹም የኢኮኖሚ አቅም በተለይ ከተጎጂ ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ በመሆኑ ለሚደርሰው ጉዳት ካሳ ቢከፍሉ አንደኛ በኢኮኖሚያዊ አቋማቸው ላይ ያን ያህል የከፋ ጉዳት አይደርስባቸውም ሌላው ደግሞ የከፈሉትን ካሳ በሚሰጡት ምርት እና አግልግሎት ላይ በዋጋ መልክ ለሕብረተሰቡ እንዲከፋፈል በማድረግ የተሻለ ፍትሀዊነት እንዲኖር ማድረግ ይችላሉ በሚል ነው።[46]

ከአደገኛ ስራዎች ጋር በተያያዘ ሌላው መርህ ይህ ስራ የመንግስት ወይም በባለስልጣን የተፈቀደለት መስሪያ ቤት ቢሆንም እንኳን ጉዳት ላደረሰው ስራ የሥራው ባለቤት ተጠያቂ ከመሆን ማምለጥ አይቻለውም።[47] ስለሆነም ተጎጂ የሥራው ባለቤት ጥፋት ያለበት መሆን አለመሆኑን ማስረዳት ሳይጠበቅበት በአደገኛ ስራው ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት በማሳየት ብቻ የስራውን ባለቤት ለጉዳቱ ኃላፊነት እንዲወስድ ማድረግ ይችላል።

ከአደገኛ ስራዎች ጋር በተያያዘ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 57904 የሰጠውን አስገዳጅነት ያለው ውሳኔ ስናይ ተጎጂ ሆነው በስር ፍርድ ቤቶች የቀረቡት ግለሰብ በአንድ ህንፃ ላይ ተቀጥረው የግንባታ ስራ በማከናወን ላይ ሳሉ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ንብረት የሆነው ክፍተኛ ጉልበት ያለው የኢሌክትሪክ ገመድ ጉዳት ያደረሰባቸው በመሆኑ የኢሌክትሪክ ገመዱን የዘረጋው የኢትዮጵያ ኢሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን፣ ተጎጂ ሲሰሩበት የነበረውን ህንፃ ባለቤት እና ቀጥሮ ያሰራቸው የነበረውን ተቋራጭ ለጉዳቱ ካሳ እንዲከፍሉ ጠይቀዋል።

ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሀይል ኮርፖሬሽን ለጉዳቱ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት አለበት በማለት ለተጎጂ ካሳ እንዲከፍል የወሰነበት ሲሆን ኮርፖሬሽኑም ይህን በመቃወም ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የስራው ተቋራጭ እና የህንፃው ባለቤት ናቸው ለጉዳቱ ተጠያቂ ሊሆኑ የሚገባቸው በማለት ይግባኙን አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የኢትዮጵያ ኢሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ለጉዳቱ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነት መውሰድ አለበት ተብሎ የተወሰነው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ትክክል አይደለም በማለት የተጎጂ አሰሪ እና ኮርፖሬሽኑ በጋራ ሃላፊነት ሊወስዱ ይገባል በማለት ወስኗል።

[46] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 91
[47] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2069(2)

በመጨረሻም ኮርፖሬሽኑ ለሰበር ሰሚ ችሎት የኤሌክትሪክ መስመሩ ጉዳት ያደረሰው የሚሠራው ህንፃ ቁመት እየጨመረ ሄዶ ወደ ኤሌክትሪክ መስመሩ በመጠጋቱና ተጎጂ ይዘውት በነበረው ፌሮ ብረት የኤሌክትሪክ መሥመሩን በመንካታቸው ነው። ተጎጂ መስመሩ ካልተነሣ ሥራውን ማቆም ይገባቸው ነበር። ስለዚህ ለደረሰው ጉዳት የህንፃው ባለቤትና የተጎጂ አሠሪ እንጂ እኛ ኃላፊ መባላችን መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት አመልክተዋል። የሰበር ሰሚ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሳኔ የሰጠ ሲሆን አስፈላጊውን የውሳኔው ክፍል የሚከተለው ነው፡-

"አመልካች በጉዳቱ ካደረሰው ጉዳት በኃላፊት የማይጠይቀው የትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2086 ንዑስ አንቀጽ 2 በሚደነግገው መሠረት ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተበዳዩ ጥፋት መሆኑን በማስረጃ በማስረዳትና በማረጋገጥ ነው። አመልካች ለጉዳቱ ኃላፊ አለመሆኑን ለማስረዳትም በመጀመሪያ የኤሌክትሪክ መሥመሩን የሚንስትሮች ምክር ቤት ስለ ኤሌክትሪክ ሥራዎች ባወጣው ደንብ ቁጥር 49/1991 አንቀጽ 35 ስለ ኤሌክትሪክ መስመሮችና መሣሪያዎች ደህንነት የደነገገውን በሚያሟላ ሁኔታ ተዘርግቶ የነበረ መሆኑንና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 41(1) መሠረት በስር ሁለተኛ ተከላሽ በነበረው ግቢ ከምድር በላይ ዘርግቶት የነበረው መስመር የአደጋ መከላከያ ፕላስቲክ ተሸፍኖ የነበረ መሆኑንና ተጠሪ ጥፋት የሆነ አደጋ የሚያስከትል ተግባር በመፈፀሙ ምክንያት አደጋው የደረሰ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 234/1/ እና 223 መሠረት ከመከላከያ መልስ ጋር ዘርዝሮ በማቅረብና የሠነድ ማስረጃዎቹን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 339/1/ በሚደነግገው መሠረት በማቅረብ የማስረዳት ግዴታውን መወጣት አለበት።"

ስለሆነም አደገኛ ስራዎችን የሚያከናውን ሰው ወይም ማንኛውም አካል በስራው በሚደርስ አደጋ ምክንያት ከሚመጣ ሃላፊነት መዳን የሚችለው ለአደጋው መድረስ የተጎጂው ጥፋት ያለበት መሆኑን ማስረዳት ከቻለ ብቻ ነው። በሌላ በኩል ተጎጂው ይህ የሥራው ባለቤት ለደረሰው ጉዳት ጥፋት ያለበት መሆኑን ማስረዳት ሳያስፈልገው በስራው ምክንያት ለደረሰበት ጉዳት ተገቢውን ካሳ የመጠየቅ መብት አለው።

3.2 በንብረት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት

በዚህ ክፍል ጉዳት ያደረሱ ንብረቶች ባለንብረት ወይም ባለይዞታ መሆን ስለሚያመጣው ኃላፊነት እንመለከታለን። ጉዳት ሲያደርሱ ኃላፊነትን የሚስያከትሉ ንብረቶች እንስሳት፣ ህንፃዎች፣ ማሽኖች እና ሞተር ተሽከርካሪዎች እንዲሁም የተመረቱ/የተሰሩ/ ዕቃዎች ናቸው።

3.2.1እንስሳት ለሚያደርሱት ጉዳት ኃላፊነት

አንድ እንስሳ ለሚያርሰው ጉዳት ኃላፊነት የሚወስዱት እንደሁኔታው የእንስሳው ባለቤት ወይም የእንስሳው ጠባቂ ሊሆኑ ይችላሉ።

የእንስሳው ባለቤት፡- ጉዳት ያደረሰ እንስሳ ባለቤት ምንም እንኳን ለጉዳቱ መድረስ የእርሱ ጥፋት ባይኖርበትም ጉዳት ያደረሰው እንስሳ ባለቤት በመሆኑ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ኃፊነትን ይወስዳል። ይህ ባለሀብት ለጉዳቱ ኃላፊነትን እንዲወስድ የሚገደደው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-[48]

- ✓ እንስሳው በድንገት ከባለቤቱ አምልጦም ይሁን ሳያመልጥ ያደረሰው ጉዳት ሲሆን
- ✓ ያደርሳል ተብሎ ያልተጠበቀውን ጉዳትም ቢሆን
- ✓ እንስሳው ጉዳት ያደረሰው በታዛዥነት ከባለቤቱ ከተረከበ ሰው ዘንድ ወይም ለባለቤቱ ወይም ለሌላ ሰው የሚሰራ ሰው ይዞታ ስር ባለበት ወቅት ከሆነ የእንስሳው ባለቤት ኃላፊነትን ይወስዳል።[49] ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰው በአደራ እንዲጠብቅ በተሰጠው ሰው ጥፋት ምክንያት ከሆነ ባለቤቱ ለጉዳቱ ተጠያቂ አይሆንም።

የእንስሳው ጠባቂ፡- የእንስሳው ጠባቂ ማለት እንስሳውን ለግል ጥቅሙ ከባለቤቱ በተውሶም ሆነ በኪራይ የተረከበ እንስሳውን ለመጠበቅ ወይም ለመቀለብ ወይም ለሌላ የግል ጉዳይ የተረከበ እና እንስሳው በራሱ ጠባቂነት ስር ያለ ሰው ነው።[50] በእንዲህ ያለ ሁኔታ እንስሳው ጉዳት ቢያደርስ አላፊ የሚሆነው እንስሳው በእጁ የሚገኘው ግለሰብ ነው።[51]

እንስሳ በሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ሲያደርስ ማን ተጠያቂ ይሆናል የሚለው ጥያቄ ከተመለሰ በኋላ እነዚህ ኃላፊነት የሚወስዱት አካላት ኃላፊነቱን በምን መልኩ ይወጡታል ለሚለው ጥያቄ ህጉ የተለያዩ መፍትሔዎችን አስቀምጧል። በዚህም መሰረት ለጉዳቱ ኃላፊነትን የሚወስደው የእንስሳው ባለቤት ከሆነ እና እንስሳው የሰው አገልጋይ ወይም የቤት እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ እንስሳውን ጉዳት ለደረሰበት ሰው በመልቀቅ ወይም ባለቤትነት በማስተላለፍ ግዴታውን መወጣት ይችላል።[52]

---

[48] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2071
[49] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2072(2)
[50] የግርጌ ማስወሻ 7 ገፅ 95
[51] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2072
[52] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2074(1)

በሌላ በኩል ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነትን የሚወስደው ጠባቂው ከሆነ ይህ ጠባቂ ጉዳቱ በደረሰበት ግዜ የነበረውን የእንስሳውን ዋጋ በመክፈል ኃላፊነቱን መወጣት ይችላል። ነገር ግን እንስሳው ጉዳት ያረሰው በባለቤቱ ወይም በጠባቂው ወይም ከሁለቱ በአንዱ ስልጣን ስር በሚተዳደር ሰው ጥፋት ከሆነ የኃላፊነት መጠኑ የእንስሳውን የባለቤትነት መብት ለተጎጂ በማስተላለፍ ብቻ የሚወሰን አይሆንም።[53] ይልቁንም የኃላፊነት ወሰኑ ከደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ስለሚሆን የፍታብሔር ተጠያቂነትን የሚወስደው አካል በደረሰው ጉዳት ልክ ተጎጂን እንዲክስ ይገደዳል።

ከተጎጂው መብት ጋር በተያያዘ እንስሳው ጉዳት ያደረሰው በተጎጂው የማይንቀሳቀስ ንብረት ለምሳሌ አዝዕርት፣ ሳር፣ እና የመሳሰሉት ላይ ከሆነ ተጎጂው የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-[54]

- ✓ የንብረቱ ባለይዞታ ወይም ጠባቂው ካሳ እስኪከፈለው ድረስ ጉዳት ያደረሰውን እንስሳ በመያዣነት የመያዝ መብት
- ✓ ከእንስሳው ግምት መጠን በላይ የሆነን ጉዳት ለማስቀረት እንስሳውን መግደል አስፈላጊ ሲሆን ተጎጂው እንስሳውን የመግደል መብት አለው። ነገር ግን ተጎጂው እነዚህን እርምጃዎች በሚወስድበት ጊዜ የተወሰደውን እርምጃ ለባለቤቱ የማስታወቅ ግዴታ አለበት።

3.2.2በህንፃ ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት

ህንፃ ማለት በዋነኝነት ማንኛውም ለሰው አገልግሎት እንዲውል የተሰራ ግንባታን የሚያጠቃልል ሲሆን ለአብነት ያህል የንግድ ህንፃዎች፣ ቤቶች፣ ድልድዮች፣ አጥሮች እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።[55]

ሕንፃዎች በተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ በሆነ ምክንያት ተደርምሰው ወይም ተንደው በሰው ወይም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ።[56] ነገር ግን እነዚህ ህንፃዎች የሚኖራቸው ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ስለሆነ መገንባታቸው አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ማንኛውም ሰው ህንፃ ሲገነባ ቀድሞ ያልነበረ የአደጋ ሁኔታ በመፍጠሩ የገነባው ህንፃ በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ሕንፃውቸን ከመገንባቱ በፊት፣

[53] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2075
[54] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2076
[55] የሕንፃ አዋጅ...
[56] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 100

በሚገነባበትና ከገነባም በኋላ ተገቢውን የእድሳት እና ሌሎች ጥንቃቄዎችን ማድረግ ይኖርበታል። ነገር ግን ይህ ህንፃ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳትን ባስከተለ ግዜ የባለቤቱ ጥፋት ቢኖርም ባይኖርም ተጠያቂነትን ያስከትላል።

የህንፃ ባለቤት ወይም ባለይዞታ ህንፃው ሊያደርስ ይችላል ተብሎ ያልታሰበ ድንገተኛ አደጋ ቢያደርስም ለጉዳቱ ኃላፊነት ይወስዳል።[57] ስለሆነም ህንፃው በመፍረስ ወይም በመደርመስ በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ቢያደርስ ያደርሳል ተብሎ ያልታሰበም ሆነ አልሆነ የህንፃው ባለቤት ወይም ባለይዞታ ጥፋት ያለበት መሆኑን ማስረዳት ሳያፈልግ ተጠያቂ ይሆናል።

ነገር ግን ይህ ጉዳት የደረሰው ህንፃውን በገነባው፣ ህንፃው ውስጥ በሚኖር ወይም በሌላ ሰው ጥፋት ምክንያት ሊሆን የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ። በዚህ ጊዜ የህንፃው ባለቤት ተጎጂውን ከካሰ በኋላ ለዚህ ጉዳት ምክንያት የሆነውን አካል መጠየቅ ይችላል።[58] በሌላ በኩል ከህንፃው ላይ በተቀመጡ ተንቀሳቃሽ ነገሮች በሌላ ሰው ላይ ጉዳት በሚደርስበት ወቅት በህንፃው ውስጥ የሚኖር ሰው ወይም በሕንፃው እየተገለገለ ያለ አካል ኃላፊነትን በመውሰድ ለተጎጂው ተገቢውን ካሳ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል።

ሌላው ህንፃዎች ከሚያደርሱት ጉዳት ጋር በተያያዘ መነሳት ያለበት ጉዳይ የኃላፊነት መጠኑ ምን ያክል ነው የሚለው ጥያቄ ሲሆን የፍታብሔር ህጉ የህንፃው ባለቤት ህንፃውን ለተጎጂው በማስረከብ ኃላፊነቱን መወጣት እንደሚችል ይደነግጋል። ነገር ግን ጉዳቱ የደረሰው በባለቤቱ ወይም በእርሱ ስልጣን ስር ባለ ሰው ጥፋት ምክንያት ከሆነ ህንፃውን በማስረከብ ብቻ ከኃላፊነት መዳን አይቻልም።[59] የዚህ ድንጋጌ ይዘት ሲታይ በአሁኑ ዘመን ያለውን የመሬት ዋጋ እና ሕንፃ ከመሬት ጋር ያለውን የማይነጣጠል ቁርኝት ግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም።

አደጋ ከደረሰ በኋላ ለጉዳቱ ካሳ ይገባኛል ብሎ ከመካሰስ ይልቅ አደጋው አስቀድሞ ሊቀለበስ የሚችልበት አግባብ ካለ ከብዙ ነገር አንፃር የተሻለ ነው። ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል ሕጉ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ቤት በሚነሳ አደጋ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ ካሰበ

[57] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2077(1)
[58] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2077(2)
[59] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2078

የቤቱን ባለቤት ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት አስቀድሞ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ የመጠየቅ መብት የሰጠው።[60]

ከሕንፃዎች ጋር በተያያዘ ኃላፊነትን የሚያስከትለው በመፍረስ ብቻ ለሚደርስ ጉዳት ሳይሆን ከሕንፃው ላይ በሚወድቁ ዕቃዎችም ጭምር ነው። በዚህ ጊዜ ኃላፊነት የሚወስደው የግድ የሕንፃው ባለቤት ሳይሆን በሕንፃው የሚኖረው ሰው ይሆናል።[61]

3.2.3 በመኪናና ሞተር ተሽከርካሪዎች ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት

ማሽኖች ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ የሰውና እና የጭነት ማመላለሻ መኪናዎች፣ በኢንዱስትሪ ወይም ሌላ ቦታ ተተክለው የሚሰሩ ማሽኖች እና ሌሎችንም ያካትታል። መኪናዎች እና ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ለሚያደርሱት ጉዳት ባለቤቱ ተጠያቂ ይሆናል። ይህ መኪና ወይም ሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት ያደረሰው ይህንኑ ለማንቀሳቀስ ወይም ለመንዳት ባልተፈቀደለት ሰው ምክንያት ቢሆንም እንኳን ባለቤቱ ከተጠያቂነት ሊያመልጥ አይችልም። ነገር ግን አደጋው በደረሰ ጊዜ ተሽከርካሪው የተሰረቀ መሆኑን ማረጋገጥ ከተቻለ ባለቤቱ ኃላፊነት አይኖርበትም።[62]

በሌላ በኩል አንድ ሰው መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪው ለግል ጥቅሙ ሊገለገልበት ከባለቤቱ የወሰደ እንደሆነ ይህ መኪና ወይም ተሽከርካሪ በእጁ በነበረበት ወቅት ላደረሰው ጉዳት ኃላፊነትን ይወስዳል። ነገር ግን መኪናውን ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪውን ለማንቀሳቀስ ወይም ለመንዳት የተቀጠረ ሰራተኛ ጉዳቱ የደረሰው በራሱ ጥፋት ካልሆነ በቀር ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ አይሆንም።[63] ስለሆነም የመኪና ወይም የተሽከርካሪው ባለቤት የቀጠረው ሰራተኛ ንብረቱን በሚያሽከረክር ወይም በሚያንቀሳቅስበት ወቅት አደጋ አድርሶ ጉዳት ቢያስከትል ኃለፊነትን የሚወስደው ባለቤቱ ይሆናል። ይህ ባለቤት ከኃላፊነት ሊያመልጥ የሚችለው የደረሰው ጉዳት በሰራተኛው ጥፋት መሆኑ ከተረጋገጠ ብቻ ነው። በዚህ ግዜ ሰራተኛው ኃላፊነት ይኖርበታል።[64]

የኃላፊነት ግንኙነቱን በተመለከተ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2083 ስር የተቀመጠ ሲሆን በዚህም መሰረት በመኪና ወይም በሞተር ተሽከርካሪ ጉዳት የደረሰበት ሰው እንደሁኔታው

[60] ዚኢ ከማሁ ቁጥር 2079
[61] ዚኢ ከማሁ ቁጥር 2080
[62] ዚኢ ከማሁ ቁጥር 2081
[63] ዚኢ ከማሁ ቁጥር 2082(1)
[64] ዚኢ ከማሁ ቁጥር 2082(2)

ተጠያቂ የሚሆኑትን ማለትም ባለቤቱን፣ ተጠቃሚውን ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛውን በአንድነት ወይም በተናጠል ሊከስ/ሊጠይቅ ይችላል። በዚህ ጊዜ የመኪናውን ወይም የባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ለተጎጂው ካሳ ይከፍል እና የከፈለውን ሙሉ ካሳ ከጠባቂው ወይም ከቀጠረው ሰራተኛ እንደሁኔታው ሊጠይቅ ይችላል።

በሌላ በኩል ተሽከርካሪዎች እርስ በእርስ ተጋጭተው አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ። ይህ በሚሆንበት ግዜ እርስ በእርስ ከተጋጩት መኪኖች መካከል አንዳቸው ለጉዳቱ ጥፋት ያለባቸው መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ እያንዳንዳቸው ለአደጋው እኩል አስተዋፅኦ እንዳደረጉ ተቆጥሮ የእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ባለቤት ወይም ጠባቂ ለደረሰው ጉዳት እኩል እንዲከፍሉ ይደረጋል። ነገር ግን አደጋው የደረሰው በአንደኛው ተሽከርካሪ ነጂ ጥፋት መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ ጥፋት የሰራው አሽከርካሪ ለጉዳቱ ሙሉ በሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳል።[65]

3.2.4 በተሰሩ እቃዎች ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር ኃላፊነት

አንድ ሰው ምርት አምርቶ ትርፍ ለማግኘት ለገበያ ቢያቀርብ እና ይህ ምርት በአግባቡ በተጠቀመው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆን የፍትሐብሔር ተጠያቂነት ይኖርበታል። አንድ ዕቃ በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችለው በምርቱ ላይ ጉድለት ያለበት እንደሆነ ነው። ስለሆነም ተሰርቶ ለገበያ የቀረበው ዕቃ በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ አምራቹ ኃላፊነትን ይወስዳል። ነገር ግን ተጎጂው አምራቹን ተጠያቂ ለማድረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

- ✓ ተጎጂ እቃውን የገዛው እቃውን ከሰራው ሰው ውጪ ከአከፋፋዩ ወይም ከቸርቻሪው መሆን አለበት። ነገር ግን ተጎጂው እቃውን በቀጥታ ከአምራቹ የገዛው እንደሆነ ጉዳቱ የሚታየው በሸያጭ ውል መሰረት ይሆናል።
- ✓ ዕቃው የተሰራ መሆን ይኖርበታል። ይህም ማለት በተወሰነ የምርት ሂደት ውስጥ በማለፍ ተፈጥሮአዊ ይዘቱን የቀየረ መሆን ይኖርበታል።
- ✓ ተጎጂ ዕቃውን ሲገዛ በልማድ እንደሚደረገው ተገቢውን ምርመራ ወይም ፍተሻ አድርጎ መሆን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነ እና ተጎጂ እቃውን ከሻጭ እጅ ሲገዛ ተገቢውን ልማዳዊ ፍተሻ ወይም ምርመራ ካላደረገ እና ጉዳቱን ያስከተለው ጉድለት በተራ ምርመራ መታወቅ የሚችል ዓይነት መሆኑ ከተረጋገጠ የዕቃው ሰሪ ተጠያቂ አይሆንም።

[65] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2084

- ✓ ተጎጂ ጉዳት የደረሰበት ዕቃውን በሚገባ ወይም ለተሰራበት ዓላማ በተገቢው ሁኔታ ሲጠቀምበት መሆን አለበት። ነገር ግን ተጎጂ ጉዳት የደረሰበት ዕቃው የተሰራበትን አላማ በመለወጥ ተጠቅሞ ከሆነ አምራቹ ተጠያቂ አይሆንም። በአጠቃላይ ከላይ የተዘረዘሩት ነጥቦች ከተሟሉ አምራቹ ያመረተው ዕቃ በሸማቹ ላይ ለሚያደርሰው ማንኛውም ጉዳት የህግ ተጠያቂነት የሚኖርበት ሲሆን እቃውን ተጠቅሞ ጉዳት የደረሰበት ማንኛውም ሸማችም ተገቢውን ካሳ የመጠየቅ መብት አለው።

3.3 ጥፋት ሳይኖር ለሚኖር ኃላፊነት የሚቀርቡ መከላከያዎች

አንድ ሰው በአስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በፈፀመው ድርጊት በሌላ ሰው መብት ወይም ጥቅም ላይ ጉዳት ሲያደርስ፣ የአደገኛ ስራዎች ባለቤት ሲሆን እና በእነዚህ ስራዎች ምክንያት ጉዳት ሲደርስ፣ የእንስሳ፣ ህንፃ፣ የባለሞተር ተሽከርካሪ እና የመኪና ባለቤት ሆኖ በእነዚህ ንብረቶች ምክንያት ጉዳት ሲደርስ እንዲሁም የአንድ እቃ አምራች ሆኖ ምርቱ ጉዳት ሲያደርስ ምንም እንኳን የፈፀመው ጥፋት ባይኖር እንዴት ኃላፊነትን እንደሚወስድ ተመልክተናል።

ይህ ጥፋት ሳይኖር ኃላፊነት በባህሪው በጣም ጥብቅ የሆነ ኃላፊነት ነው። በመሆኑም በእንስሳት፣ በሕንፃዎች፣ በመኪናዎች ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ወይም በፋብሪካ ተሰርተው በወጡ ነገሮች ምክንያት ጉዳት በሚደርስበት ግዜ ሕጉ ኃላፊ የሚያደርጋቸው አካላት ጥፋት አልሰራንም፣ የጉዳቱ ምክንያት አይታወቅም፣ ጉዳቱን ለመከላል አልቻልንም ወይም ጉዳቱ የደረሰው በሌላ ሶስተኛ ወገን ጥፋት ነው በማለት ከኃላፊነት ማምለጥ አይችሉም።[66] ስለሆነም ተጎጂ የደረሰበትን ጉዳት እና ጉዳት ያደረሰበትን ንብረት በማስረዳት ህጉ ኃላፊ ከሚያደርጋቸው ሰዎች ተገቢውን ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው ሲሆን በመርህ ደረጃ ተጎጂ እነዚህ ኃላፊነት የሚወስዱ ሰዎች ጥፋት ያለባቸው መሆኑን ማስረዳት አይጠበቅበትም።

በሌላ በኩል ህጉ እንድ ሰው ከውል ውጪ በሚመነጭ ኃፊነት ክስ ቢቀርብበት ምን ምን መከላከያዎችን ማቅረብ ይችላል የሚለውን ቀጥለን እንመልከት፡-

ሀ) የተጎጂው ጥፋት፡- በእንስሳት፣ በህንፃዎች፣ በማሽኖች እና በሞተር ተሽከርካሪዎች ወይም በተመረቱ ዕቃዎች አማካይነት ጉዳት ሲደርስ ለጉዳቱ ኃላፊነት እንዲወስድ ሕጉ ግዴታ የጣለበት አካል ጉዳቱ የደረሰው በሙሉ ወይም በከፊል በተጎጂው ጥፋት መሆኑን ማስረዳት

[66] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2086(1)

ከቻለ ተጠያቂነት አይኖርበትም።[67] ይህ መከላከያ በተጨማሪም በአስፈላጊ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ በሰው መብት ላይ ጉዳት በሚደርስ ግዜ ወይም በሰው አካል ላይ ጉዳት በማድረስ ሊነሱ ለሚችሉ ክሶች መነሳት የሚችል ነው።

ለ) የውል ግንኙነቶች፡- ሌላው እንደመከላከያ መነሳት የሚችለው የውል ግንኙነት ነው። ይህም ተጎጂ ጉዳት ካደረሰው አደገኛ ኢንዱስትሪ፣ እንስሳ፣ ህንፃ ሞተር ተሽከርካሪ እና መኪና ወይም ምርት/ዕቃ/ ባለቤት ወይም በህግ ኃላፊነት ካለበት ሰው ጋር የተዋዋለ እንደሆነ ከላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ጉዳት ደርሶብኛል በማለት ከውል ውጪ ያለ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ካሳ መጠየቅ አይችልም። እንዲህ በሆነ ግዜ ጉዳዩ የሚወሰነው ባለቤቱ እና ተጎጂ በፈፀሙት ውል መሰረት ነው።[68]

ለምሳሌ በአደገኛ ኢንዱስትሪዎች ተቀጥረው የሚሰሩ፣ በህንፃዎች ተቀጥረው የሚሰሩ ወይም ተከራይተው የሚኖሩ ሰዎች ወይም ሌላ ተመሳሳይ የውል ግንኙነት ከንብረቱ ባለቤት ጋር ያላቸው ግለሰቦች በእነዚህ ንብረቶች ምክንያት ጉዳት ቢደርስባቸው በህጉ ንብረቶቹ ጉዳት ቢያደርሱ ስለሚኖር ኃላፊነት የተደነገጉ አንቀፆችን ጠቅሰው ካሳ መጠየቅ አይችሉም። ይህ ማለት ግን ለደረሰባቸው ጉዳት ምንም ዓይነት ካሳ የመጠየቅ መብት የላቸውም ማለት አይደለም። ይልቁንም እንዲህ ዓይነት የውል ግንኙነት በሚኖርበት ጊዜ የጉዳቱን ኃላፊነት ስለሚወስድ ሰው እና የጉዳቱ ካሳ መጠን የሚወሰነው በውሉ መሰረት ይሆናል።

ሐ) ጥቅም የሌለው ግንኙነት፡- ማንኛውም ሰው በህንፃ፣ በእንስሳ ወይም በሌላ ነገር ሲጠቀም ጉዳት ቢደርስበት ምንም እንኳን ከባለቤቱ ወይም ከጠባቂው ጋር ምንም ዓይነት የውል ግንኙነት ባይኖረውም ከውል ውጪ በሚኖር ኃላፊነት ባለቤቱን ወይም ጠባቂውን መክሰስ የሚችለው ይኸው ባለቤት ወይም ጠባቂ ከንብረቱ አንዳች ጥቅም የሚያገኝ ከሆነ ብቻ ነው።[69] ይህም ማለት በንብረቶቹ ሲጠቀም ጉዳት የደረሰበት ሰው ከውል ውጪ ያለ ኃላፊነት ድንጋጌዎችን ጠቅሶ ለካሳ ክፍያ መከራከር የሚችለው ጉዳት ባደረሱት ንብረቶች ሲጠቀም ለባለቤቱ ወይም ለጠባቂው ክፍያ ይፈፅም ወይም ሌላ ጥቅም ያስገኝ ከነበረ ነው። ይህ ካልሆነ እና ለባለቤቱ ወይም ለጠባቂው ምንም አይነት ጥቅም ሳያስገኝ በንብረቶቹ ሲጠቀም ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከውል ውጪ ባለ ኃላፊነት መክሰስ አይችልም። የንብረቶቹ ባለቤት ወይም

[67] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2086(2)
[68] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2088
[69] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2089

ጠባቂም ተጎጂ ጉዳት የደረሰበት ምንም ዓይነት ጥቅም በማያገኝበት ሁኔታ ጉዳት ያደረሱትን ንብረቶች ተጎጂ ሲጠቀም በነበረበት ግዜ መሆኑን በማስረዳት ከኃላፊነት መዳን ይችላል።

4. ለሌሎች ኃላፊ ስለመሆን (Vicarious Liability)

ይህ ኃላፊነት በእንግሊዝኛው /vicarious liability/ የሚባለው ሲሆን ሌላ ሰው ላስከተው ጉዳት ኃላፊነቱን የመወጣት ግዴታ የሚወድቀው በሌላ ሰው ላይ መሆኑን የሚያሳይ የከውል ውጪ ኃላፊነት አንዱ መገለጫ ነው።[70] በፍትሐብሔር ሕጋችን ከቁጥር 2124 እስክ 2136 ስር ተደንግጎ እናገኘዋለን። ኃላፊነትን የሚያስከትለው ተግባር የተፈፀመው በሌላ ሰው ሲሆን ተጠያቂ የሚሆነው ግን ሌላ ሰው ነው። ኃላፊነት የሚያስከትለውን ተግባር የሚያከናውኑት ሦስት ዓይነት ሰዎች ናቸው። እነሱም አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ፣ ሠራተኛ እና ደራሲያን /ፀሐፊዎች/ /authors/ ናቸው። ሠራተኛ የሚለው የመንግስት ሹም ሠራተኛ ወይም ሌሎች ሠራተኞች ሊመለከት ይችላል። ለአካለመጠን ላልደረሰ ልጅ ኃላፊ የሚሆኑት ወላጆችና ሌሎች ሲሆኑ ለሠራተኛ ደግሞ መንግስት ወይም አሠሪ ይሆናሉ። ለደራሲ ኃላፊ የሚሆነው አሳታሚው ነው።[71]

ሌሎች ላደረሱት ጉዳት ኃላፊነቱን ለምን እንዲወስዱ ይደረጋል? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ ምክንያቶች ይሰጣሉ። ከነዚህም መካከል፡-[72]

- ✓ የመቆጣጠር ችሎታና አቅም ስላላቸው ለምሳሌ ወላጆች የልጆቻቸውን ባሕሪ እየቀረፁ የማሳደግ ግዴታ ሲኖርባቸው አሰሪዎችም ለሰራተኞቻቸው ተገቢውን የስራ አቅጣጫ ሰጥተው የማሰራት ኃላፊነት አለባቸው
- ✓ የድርጊቱ መንስኤ እነሱ ስለሚሆኑ ኃላፊነቱንም መውሰድ ያለባቸው እነሱ ናቸው ከሚል ምክንያት በመነሳት ለምሳሌ ስራው እንዲሰራ የፈለገው፣ ያዘዘው፣ የመስሪያ ቁሳቁስ ያቀረበው አሰሪው በመሆኑ በስራው ምክንያት ለሚደረስ ጉዳት ዋነኛው መንስኤ አሰሪው በመሆኑ እሱ ተጠያቂ መሆን አለበት የሚል አስተሳሰብ ነው።
- ✓ የተሻለ ኢኮኖሚያዊ አቅም ያላቸው ስለሆኑ ለምሳሌ ወላጆች ከልጆች፣ አሰሪዎች ከሰራተኞች፣ አሳታሚዎች ከደራሲዎች የተሻለ የመክፈል አቅም ስለሚኖራቸው ኃላፊነቱን እነሱ ላይ ቢጫን ይሻላል ከሚል አስተሳሰብ የተነሳ፣

[70] የግርጌ ማስታወሻ 7 ገፅ 110
[71] ዚኒ ከማሁ
[72] ዚኒ ከማሁ ገፅ 110-113

- ✓ የተሻለ ጥቅም የሚያገኘው አካል ጉዳቱንም እሱ ራሱ መሸፈን አለበት ከሚል አስተሳሰብ ለምሳሌ አንድ አሰሪ ከሚሰራው ስራ የሚያገኘው ጥቅም ከማንኛውም አካል (በተለይም ከሰራተኛው) የተሻለ ስለሆነ የመሳሰሉት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

4.1 የወላጆች ኃላፊነት

የፍትሐብሔር ሕጉ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ኃላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሰራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኩል ለተሠራው ሥራ ኃላፊ የሚሆነው አባት ነው በማለት ቅድሚያ አባትን ያስቀምጠዋል።[73] ለዚህ የሚሰጠው ምክንያት አባት የቤተሰቡ እራስ፣ የቤተሰቡ ሹም ወይም መሪ መሆኑ በሕግም ጭምር እውቅና የተሰጠው ስለነበር ነው።[74] ይህ ግን የኢፌዳሪ ሕገ-መንግስትንም ሆነ የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕጐችን የሚፃረር ነው። ለምሳሌ በኢፌዳሪ ህግ መንግስት መሠረት ባል እና ሚስት በጋብቻ ዘመን እኩል መብት ሲኖራቸው በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው።[75] ይህም በመሆኑ ባልና ሚስት ልጆቻቸው በመልካም ስነምግባር እንዲታነፁ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ ለማድረግ መጣር አለባቸው።

ስለሆነም አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ኃላፊ በሚሆንበት ጊዜ አባትና እናት እኩል ኃላፊ መሆን አለባቸው እንጂ በመጀመሪያ ደረጃ አባት በሁለተኛ ደረጃ እናት መሆን የለባቸውም። በዚህ ረገድ የፍትሐብሔር ሕጉ ከኢፌዲሪ ሕገ መንግስትና ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንፃር መቃኘት አለበት።

ልጆች ለሚያድርሱት ጉዳት ግን ሁሌም የልጁ ወላጆች ብቻ አይደሉም ኃላፊነት የሚኖርባቸው። ኃላፊነትን ለመጣል አስቀድሞ ልጁ በማን ቁጥጥር ወይም አሳዳጊነት ስር እንዳለ ማረጋገጥ ያስፈልጋል። በዚህም መሰረት ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ልጁ በሌሎች አሳዳጊዎች ስር ከነበረ አሳዳጊዎቹ፣ ትምህርት ላይ ሳለ ከሆነ አስተማሪው፣ ስራ ላይ ከነበረ አሰሪው ኃላፊነትን የሚወስዱ ይሆናል።[76]

---

[73] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2124
[74] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 635 እና 636
[75] የግርጌ ማስታወሻ 1 አንቀፅ 34(1) እና የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀፅ 50
[76] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2125

4.2 የመንግስት ኃላፊነት

የመንግስት ሹም ወይም ሠራተኛ በራሱ ጥፋት በሌላው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ኪሣራውን ለመክፍል ይገደዳል። ይህ ጥፋት በሁለት አጋጣሚ ሊደረግ ይችላል። አንድ አጋጣሚ የመንግስትን ሥራ ሲሠራ ሊሆን ይችላል። የግል ሥራውን ሲሠራም ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው ጥፋት የሥራ ጥፋት ሲሆን የተጎዳው ሰው ካሳ ከመንግስት ላይ ለመጠየቅ ይችላል። ሠራተኛው ያደረገው ጥፋት የግል ጥፋቱ የሆነ እንደሆነ ግን መንግስት ኃላፊነት አይኖርበትም።[77] አንድ ጥፋት የሥራ ጥፋት ለመባል የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-[78]

- ✓ ሥራው በስልጣኑ ልክ መሆን አለበት
- ✓ በቅን ልቦና የተደረገ መሆን አለበት
- ✓ ለሥራ ክፍል ወይም ለመንግስት ጥቅም ሲባል የተሰራ መሆን አለበት

ከዚህ ውጭ በሆነው በማናቸውም ሌላ ጉዳይ ጥፋት ቢፈፀም ጥፋቱ እንደግል ጥፋት ሆኖ ይቆጠራል።

ከላይ የተገለፁት ነጥቦችና ሀሳቦች በሙሉ ለክልል መንግስታት ሠራተኞችና ለህዝብ አገልግሎት በተቋቋሙ በሕግ የሰውነት መብት በተሰጣቸው ድርጅቶች ሠራተኞችም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።[79]

4.3 የአሰሪዎች ኃላፊነት

"አሰሪ" ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ በራሱ መሪነት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውልን በመመስረት ደመወዝ እየከፈለ የሚያሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት ነው።[80] አንድ ሠራተኛ ሥራውን የሚሰራበት ጊዜ ኃላፊነትን የሚያስከትል ጥፋት የሰራ እንደሆነ በፍትሐብሔር በኃላፊነት የሚጠየቀው አሰሪው ይሆናል።[81] ሠራተኛው በሚሰራበት ቦታና ጊዜ የጥፋት ተግባር የፈፀመ እንደሆነ

[77] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2126
[78] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2127
[79] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2128 እና 2129
[80] የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 2(1) እና 4
[81] የግርጌ ማስታወሻ 5 ቁጥር 2130

ጉዳቱን ሥራውን በማከናወን ላይ ሳለ እንደሰራው ይቆጠራል በማለት "ሥራውን በሚሠራበት ጊዜ" የሚለውን ሐረግ ሕጉ የሕሊና ግምት ወስዷል።[82]

ማጠቃለያ

ሰዎች በተለያየ ምክንያት በሌሎች ላይ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ ወይም ቁሳዊ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ። እንዲህም በሆነ ጊዜ ጉዳት ያደረሱበትን አካል በከውል ውጪ ኃላፊነት ሕግ መሰረት ለጉዳቱ ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ የመክፈል ግዴታ አለባቸው። ከውል ውጪ ኃላፊነት የፍትሐብሔራዊ ኃላፊነት አንድ ዘርፍ ሲሆን ዋነኛ ዓላማውም የተጎዳን አካል በሕግ አግባብ ካሳ እንዲያገኝ ማስቻል ነው።

የከውል ውጪ ኃላፊነት የሚኖረው የግድ ጉዳት አድራሹ እራሱ ላደረገው ጉዳት አይደለም። ጥፋት ማጥፋትም የግድ ላይጠበቅበት ይችላል። በከውል ውጪ ኃላፊነት መሰረት አንድ ሰው ኃላፊነት ሊወስድ የሚችለው በሦስት ምክንያቶች ነው። አንደኛው ጥፋት ሳይኖር የሚኖር ኃላፊነት ሲሆን ጉዳቱ የደረሰው በሱ መሆኑ ብቻ ከተረጋገጠ ጥፋት ባይኖርበትም እንኳን ካሳ

[82] ዚኒ ከማሁ ቁጥር 2132

የመክፈል ኃላፊነት ይኖርበታል። ሁለተኛው ጥፋት ላይ የተመሰረተ ኃላፊነት ሲሆን ጉዳት አድራሹ ጥፋት ሲኖርበት ብቻ ኃላፊነት እንዲወስድ የሚደረግበት ስርዓት ነው። በመሆኑም በዚህ ስር አንድን ሰው ኃላፊ ነው ለማለት በመጀመሪያ ጥፋተኝነቱን ማረጋገጥ ይጠበቅብናል ማለት ነው። ሦስተኛውና የመጨረሻው ለሌሎች ስለሚኖር ኃላፊነት ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው እንዲሁም አሰሪዎች ለሰራተኞቻቸው የሚኖርባቸውን ኃላፊነት የሚመለከት የኃላፊነት ምንጭ ነው።

ዋቢ

1. **የኢፌድሪ ሕገ-መንግስት**
2. **የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግስት የፍትሐብሔር ሕግ**
3. **የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር** 1156/2011
4. Abdulmalik Abubeker & Desta G/Michael, *Extra-Contractual Liability Teaching Material*, (2009)
5. **የፌደራል የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል፣ ስለቅድመ ስራ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል፣ *የተሸሻለው ከውል ውጭ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊነት***
6. Bryan A. Garner, Black's Law Dictionary, 8th ed. (2004)
7. https://www.nascollege.org/e%20cotent%2010-4-20/dr%20chandan%20uadhyay/Law%20of%20Torts.pdf (Accessed on 07 Dec. 2022)

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

+251115-51-50-99

6044

0115-51-77-75

1370

info@eag.gov.et

የፍትሕ ሚኒስቴር
MINISTRY OF JUSTICE

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia